# 1. የመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር የሚመራባቸው የሕግ ማዕቀፎችና የአፈፃፀም ሰነዶች

1.1 የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት የግዥ እና ንብረት አስታዳደር ሥርዓት ለመወሰንና ለመቋጣጠር የወጣ አዋጅ ቁጥር 87/2002፤

## 1.2 መመሪያች

- የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት የግዥ መመሪያ
- የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት የንብረት አስተዳደር መመሪያ

## 1.3 መደበኛ የጨረት ሰነዶች

የመንግስት ግዥ አፈጻጸም ግልፅና ቀልጣፋ በማድረግ በብሔራዊ እና በዓለም አቀፍ ደረጃ ለሚፈፀሙ ግዥዎች የሚያገለግሉ የሚከተሉት መደበኛ የጨረታ ሰነዶች ሥራ ላይ ዉለዋል

- ለዕቃ ግዥ
- ለግንባታ ዘርፍ ሥራ ግዥ
- ለምክር አገልግሎት ግዥ
- ሌሎች አገልግሎቶች ግዥ
- ለማዕቀፍ ግዥ
- የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ግዥ
- የመማሪያ መጽሐፍ ግዥ

## 1.4 ማንዋሎች

- የግዥ አፈፃፀም ማንዋል
- የቋሚ ንብረት አሰታዳደር ማንዋል
- የስቶክ አስተዳደር ማንዋል
- የማዕቀፍ ግዥ ማንዋል
- የግዥ ኦዲት ማንዋል
- የግዥ ንብረት አቤቱታ ማጣሪያ ማንዋል

## 2. የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር መርሆች

<u>የመንግሰት ግዥ አፈፃፀም እና የንብረት አስተዳደር መርሆች የሚከተሉት ናቸው</u>

2.1 በግዥ አፈፃፀም ረገድ የመንግሰት ገንዘብ ሊያሥገኝ የሚችለውን ጥቅም ማስገኙቱን ማረጋገጥ

2.2 በአዋጅ በተፈቀደው ልዩ አስተያየት ካልሆነ በስተቀር በዜግነት ወይም ከመወዳደሪያው መስፈርቶች ጋር ባልተያያዙ ሌሎች ምክንያቶች በዕጩ ተወዳዳሪዎች መካከል አድልዎ አለማድረግ

2.3 ማናቸውም የግዥ ውሳኔ የሚሰጠውን ውሳኔ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ሁሉ ግልጽ እና ፍትሀዊ ማድረግ

2.4 ውሳኔዎች እና የተወሰዱ እርምጃዎች ተጠያቂነት የሚያስከትሉ መሆናቸውን ማወቅ

2.5 የመንግስት ንብረት በጥንቃቄ መያዝና ለታለመለት ዓላማ ብቻ ማዋል

2.6 በአዋጅና በዚህ መመሪያ መሠረት በተፈቀደው ልዩ አስተያየት መሠረት የሀገሪቱን ኢኮኖሚ የሚደግፍ የሀገር ውስጥ አምራቾችን ኩባንያዎችንና አነስተኛና ጥቃቅን ኢንዱስትሪዎችን ማበረታታት

2.7 የመንግስት ግዥ አፈጻጸም ቀልጣፋና ውጤታማ በማድረግ የሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ ዕደገት መደገፍ

## 3. ለመንግስት ግዥ አፈፃፀም የተፈቀዱ የግዥ ዘዴዎች

ቀጥሎ ተዘረዘሩት ስድስት የግዥ ዘዴዎች ተፈቅደዋል

**3.1 ግልጽ ጨረታ**

**3.2 የሁለት ደረጃ ጨረታ**

**3.3 የመወዳደሪያ ሃሳብ በመጠቅ የሚፈፀሙ ግዥ**

**3.4 ውስን ጨረታ**

**3.7 በዋጋ ማቅረቢያ የሚካሄድ ግዥ**

**3.6 ከአንድ አቅራቢ የሚፈፀም ግዥ**

## 4. በመንግስት ግዥ ለመሳተፍ በዕጩ ተወዳዳሪዎች መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች

በግዥ አፈጻጸም መመሪያ አንቀፅ 32 መሰረት በመንግስት ግዥ ለመሳተፍ የሚፈልጉ ዕጩ ተወዳዳሪዎች በስራ ሂደቱ ያቅራቢነት ሊስት ዳታ ቤዝ ላይ ለአቅራቢዎች ምዝገባ በተዘጋጀው ቅጽ መሰረት በቅድሚያ መመዝገብ አለባቸው፡፡ ለመመዝገብ መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

4.1 አቅራቢው የተሰማራበት የሥራ ዘርፍ ሚገልጽ የታደሰ ንግድ ፈቃድ

4.2 በግንባታ ሥራ ላይ የተሰማራ ከሆነ የሥራ ተቋጭነት ሥራ እንዲሰራ በሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር የተሰጠውን ደረጃ የሚገልፅ ማስረጃ

4.3 የምክር አገልግሎት በመስጠት ሥራ ላይ የተሰማራ አቅራቢ ከሆነ ሰለተሰማረበት የሙያ ዘርፍ ከሚመለከተው አካል የተሰጠው የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ማስረጃ

4.4 የተሽከርካሪ ጥገና አገልግሎት በመስጠት ሥራ ላይ የተሰማራ ከሆነ ከትራንስፖርት ጽ/ቤት የተሰጠውን ደረጃውን የሚገልፅ ማስረጃ

4.5 መድሐኒት እና የህክምና መገልገያ መሣሪያዎች በማቅረብ የተሠማራ ከሆነ ከመድሐኒት አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን የተሰጠውን ማስረጃ

## 5. ዋስትና በአዋጅና በአፈፃፀም መመሪያው መሠረት የሚከተሉት ዋስትና ዎች ሥራ ላይ እንዲውሉ ተፈቅደዋል

### 5.1 የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና

- የመንግስት መ/ቤቱ የጠቅላላ ግዥውን ግምታዊ ዋጋ መሠረት በማድረግ ከ 2% ያላነሰና 5% ያልበለጠ ተጫራቹ በመረጠው የዋስትና ዓይነት የሚቀርብ የጨረታ ማስከበሪያ የገንዘብ  መጠን ወስኖ በጨረታ ጥሪው እና በጨረታ ሰነዱ ውሰጥ መግለፅ ይኖርበታል ፡፡ በዚህም መሠረት የሚወሰነው የጨረታ ማስከበሪያ መጠን ከብር 500,000.00 የበለጠ መሆን የለበትም
- በግንባታ ዘርፍ የተሰማሩ የአገር ውስጥ ሥራ ተቋራጮች ለጨረታ ማስከበሪያ በሁኔታ ላይ የተመሰረተ የመድህን ዋስትና ቢያቀርብ ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

### 5.2 የውል ማስከበሪያ ዋስትና

አሸናፊ ተጫራቾች የውሉን ዋጋ ቢያንስ 10% በውል ማስከበሪያ ለመ/ቤቱ ማስያዝ አለበት፡፡

- ከአገር ውስጥ የግንባታ ዘርፍ ሥራ ተቋራጮች ወይም መድሐኒት እና የህክምና መሣሪያዎች አምራች ድርጅቶች ለሚፈጸም ግዥ ከታወቀ መድን ድርጅት የሚቀርብ በሁኔታ ላይ የተመሰረተ የውል ማስከበሪያ ተቀባይነት ይኖረዋል
- የምክር አገልግሎት በመስጠት ተግባር ላይ የተሰማሩ አማካሪዎች የሚሰጡት የምክር አገልግሎት ሂደት ውስጥ በመ/ቤቱ ላይ ጉዳት ሊያደርስ ይችላል ተብሎ ሲገመት የባለሙያ የካሣ መድህን እንያቀርቡ መጠየቅ ይችላል
- ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት በግዥ አፈጻጸም መመሪያው አንቀጽ 15.20.5/ሐ/ በተገለጸው መሰረት በጨረታ ማስከበሪያ በውል ማስከበሪያ እና በቅድሚያ ክፍያ ምትክ ካቋቋማቸው አካል የሚሰጣቸውን የዋስትና ድብዳቤ በማቅረብ መገልገል ይችላሉ
- የመድን አገልግሎት ግዥ ለመፈፀም በወጣ ጨረታ አሸናፊ የሚሆን የመድን ድርጅቶች በኢትዮጲያ ብሔራዊ ባንክ ለመጠባበቂያ ያስቀመጡትን ገንዘብ በውል ማስከበሪያነት ለመጠቀም ይችላል፡፡ ሆኖም በዚህ መንገድ ለሚያስይዙት ዋስትና በቂ መጠባበቂያ ያላቸው ስለመሆን ከባንኩ ማረጋገጫ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

### 5.3 የቅድሚያ ክፍያ ዋስትና

- በመንግስት ግዥ አፈጻጸም በማንኛውም ሁኔታ ከውል ጠቅላላ ዋጋ ከ30% በላይ የቅድሚያ ክፍያ ሊሰጥ አይችልም ፤ አቅራቢው በመንግስት መ/ቤቱ ለሚከፈለው የቅድሚያ ክፍያ ተመጣጣኝ ዋስትና ማስያዝ ይኖርበታል

## 6. ልዩ አስተያየት

በግዥ አፈፃፀም መመሪው አንቀፅ 15.15/1/ መሠረት በአገር ውስጥ የሚመረቱ ምርቶችን እና በኢትዮጲያ ኩባንያዎች የሚሰጡ የግንባታ ሥራ እና የምክር አገልግሎት ለማበረታታት የሚከተሉት ልዩ አስተያየቶች ተፈቅደዋል

6.1 በኢትዮጲያ ውስጥ ለተመረቱ ዕቃዎች 15%

6.2 በአነስተኛ ጥቃቅን ተቋማት አዋጅ መሰረት ለተቋቋሙ አነስተኛ ጥቃቅን ተቋማት ለአገር ውስጥ ግዥ 3%

6.3 በኢትዮጲያ ኩባንዎች ለሚከናወኑ የግንባታ ዘርፍ ሥራዎች 7.5%

6.4 በኢትዮጲያ ኩባንዎች ለሚከናወኑ የምርት አገልግሎት ግዥዎች 7.5%

6.5 በአገር ውስጥ ለተመረቱ መድሃኒቶችና የህክምና መሣሪያዎች 25%

ከላይ የተጠቀሱት ልዩ አስተያየት ተግባራዊ የሚሆንው የሚከተሉትን ሁኔታዎች ሙሉ በሙሉ ሲያሟላ ይሆናል፡፡

ማናቸውም የግንባታ ዘርፍ ወይም የምክር አገልግሎት ሥራ በንዑስ አንቀጽ2 (ሐ) መሠረት የተፈቀደው ልዩ አስተያየት ተጠቃሚ ሊሆን የሚችለው የሚከተሉት ሁኔታዎች በሙሉ ሲሟሉ ይሆናል

ሀ/ ኩባንያው በኢትዩጲያ ሕግ መሠረት የተቋቋመ እና ዋና መ/ቤቱ በኢትዩጰያ ውስጥ የሚገኙ ሲሆን

ለ/ ከኩባንያው አክሲዩን ወይም የካፒታል ድርሻ ከ50% በላይ በኢትዩጲያዊያን የተያዘ ከሆነ

ሐ/ ከኩባንያው የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት መካከል ከ50% በላይ ኢትዩጲያዊያን ከሆኑ

መ/ ከኩባንያው ቁልፍ ሠራተኞች  መካከል ቢያንስ ከ50% ኢትዩጲያዊያን ከሆነ

በአነስተኛ ጥቃቅን ተቋማት አዋጅ መሠረት የተቋቋሙት አነስተኛና ጥቃቅን ተቋማት

ሀ/ ከአገር ውስጥ አቅራቢዎች ጋር በሚያደርጉት ውድድር 3% ልዩ አስተያየት ይደረግላቸዋል፡፡

ለ/ ግዥው በዓለም አቀፍ የግዥ ዘዴ የሚፈፀም ሲሆን በንዑስ አንቀፅ 2(ሀ፣ለ እና ሐ) ላይ የተፈቀደው ልዩ አስተያየት ብቻ ተፈጻሚ ይደረጋል

ሐ/ በጨረታ ማስከበሪያ ፤የውል ማስከበሪያ እና የቅድሚያ ክፍያ ዋስትና ምትክ ተቋማቱን ካዳራጀ አካል በሚሰጥ ዋስትና ደብዳቤ ተቀባይነት ይኖረዋል

መ/ ለጨረታው የተዘጋጀውን የጨረታ ሠነድ በአነስተኛ እና ጥቃቅን ተቋምነት የተቋቋሙበትን የህጋዊነት ማስረጃ በማሳየት ያለ ክፍያ በነፃ ይሠጣቸዋል፡፡

## 7. እጩ ተወዳደሪዎች /ተጫራቾች በግዥ ፈጻሚዎች ላይ ቅሬታ ቢኖራቸው አቤቱታ የሚቀርብበት ሁኔታ

7.1 በግዥ ፈጻሚ መ/ቤት በአግባቡ ባለመፈጸሙ ምክኒያት ጉዳት ወይም ኪሳራ ደርሶብኛል ወይም ሊደርስብኝ ይችላል የሚል ተጫራች በግዥ አዋጅ አንቀጽ 68 እና 69 መሰረት

7.2 ዕጩ ተወዳደሪዎች በአቤቱታው መሰረት የሆነውን ውሳኔ ካወቁበት ወይም ማወቅ ይገባው ከነበረበት ቀን ጀምሮ ባሉት አምስት የስራ ቀናት ውስጥ አቤቱታውን በመጀመሪያ ግዥውን ሊፈጽመው ለመንግስት መ/ቤት የበላይ ኃላፊ ሊቀርብ ይችላል፡፡

7.3አቤቱታው በተጫራቹና በመንግስት መ/ቤቱ ስምምነት ካልተፈታ በስተቀር የመ/ቤቱ የበላይ ኃለፊ አቤቱታው በቀረበለት በ10 የስራ ቀናት ውስጥ ውሳኔውን በጽሑፍ መስጠት አለበት፡፡

7.4የመንግስት መ/ቤት የበላይ ኃላፊ በአሥር  የስራ ቀናት ውስጥ ውሳኔ ካልሰጠ ወይም ውሳኔውን መስጠት ከሚገባው ከ10ኛው ቀን በኋላ ወይም የኃላፊው ውሳኔ ያላረካው ከሆነ የኃላፊው ውሳኔ ከተገለጸበት ቀን ጀምሮ በአምስት የስራ ቀናት ውስጥ ለግዥና ንብረት አወጋገድ አቤቱታ አጣሪና ውሳኔ ሰጪ ቦርድ አቤቱታ ሊቀርብ ይችላል፡፡

7.5 ከዚህ በላይ የተገለጸው እንደተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ተጫቾች የቴክኒክና የዋጋ ማወዳደሪያ ያላባቸውን በተለያዩ ኢንቨሎፕ እንዲያቀርቡ በተደረገበት ጨረታ፣የቴክኒክ የመወዳደሪያ ሃሳብ ግምገማ ተፈላጊውን ነጥብ ባለማግኘቱ ከጨረታው ውጪ የተደረገ መሆኑ በጽሁፍ የተገለጸለት ተጫራች የተጫራቾች የዋጋ መወዳደሪያ ሃሳብ ከመክፈቱ በፊት አቤቱታውን ለመንግስት መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ  ሊያቀርብ ይችላል፡፡

7.6በቀረበው አቤቱታ ላይ በመንግስት መ/ቤቱ በተሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘና አፈጻጸሙ ሥርዓቱን ተከትሎ አለመፈጸሙን ማረጋገጥ የቻለ ተጫራች የመ/ቤቱን የበላይ ኃላፊ ውሳኔን ባወቀ በአምስት የስራ ቀናት ውስጥ አቤቱታውን ለቦርድ ሊያቀርብ ይችላል፡፡ ለቦርዱ አቤቱታ የቀረበ ከሆነ መ/ቤቱ ቦርዱ የመጨረሸ ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ የዋጋ መወዳደሪያ ሀሳብ የያዘውን ኢንቨሎፕ ሳይከፍት እንደታሸገ ማቆየት ይኖርበታል፡፡

7.7የመንግስት መ/ቤት  የጨረታውን ውጤት ወይም ለቀረበለት አቤቱታ ምላሽ በተሰጠ 7የስራ ቀን ጊዜ ውስጥ ውል መፈጸም የለበትም፡፡

7.8ጨረታውን ባወጣው የመንግስት መ/ቤት ወይም በቦርዱ ውሳኔ ቅር የተሰኘ ተጫራች ጉዳዩን አግባብ ላለው ፍርድቤት ሊያቀርብ ይችላል፡፡

## 8. አቤቱታ የማይቀርብባቸው ሁኔታዎች

8.1በግዥና በንብረት አስተዳድር አዋጅ የተዘረዘሩትን ሁኔታዎች መሠረት በማድረግ በተወሰነው የግዥ ዘዴ ምርጫ ላይ፤

8.2በውስን ጨረታ እና በዋጋ ማቅረቢያ ለሚፈጸም ግዥ በተከናወነ የተጫራቾች አመራረጥ ወይም በጨረታ ሠነዱ ላይ አስቀድሞ በሰፈረ የተጫራቾች ማወዳደሪያ መስፈርት ላይ፤

8.3በአዋጁ አንቀጽ 18 እና በዚህ መመሪያ አንቀጽ 15.15.1 መሰረት በአገር ውስጥ አቅራቢዎች፤ምርቶች እና የግንባታ ዘርፍ ስራዎች በተሰጠው ልዩ አሰተያየት ላይ ፤

8.4በአዋጅ አንቀጽ 23 መሰረት ጨረታን፤የመጨረቻ ሰነድን ወይም የዋጋ ማቅረቢያን ውድቅ ለማድረግ በተሰጠው ውሳኔ ላይ፤

8.5መ/ቤቶች የግምገማውን ውጤት ካሳወቀበት ወይም ለቀረበለት አቤቱታ ውሳኔውን በጽሁፍ ከሰጠበት ቀን ጀምሮ የሚቆጠር 5 /አምስት/ የስራ ቀን ካለፉ

8.6አቤቱታ የቀረበው ውል ከተፈረመ እና ውል በአዋጅ አንቀጽ 39 ንዑስ አንቀጽ 3 እና በግዥ አፈጻጸም መመሪያው አንቀጽ44.1 ፍደል ተራ ‹‹ሀ›› የተጠቀሰውን 7 የሥራ ቀናት የጊዜ ገደብ ጠብቆ የተፈረመ ከሆነ፤

## 9. የግዥ ፈጻሚ መ/ቤቶች በአቅራቢዎች ላይ የጥፋተኝነት ሪፖርት የሚያቀርቡበትና ቦርዱ እርምጃ የሚወስድባቸው ሁኔታ

9.1 የመንግስት መ/ቤቶች በተጫራቾች ወይም አቅራቢው ላይ የጥፋተኝነት ሪፖርት ለቢሮው ሲያቀርብ የአቤቱታውን ጭብጥ የሚገልጽ መግለጫ፤ ግዥ የተካሄደባቸውን ሰነዶች ቅጂና ሌሎች ጉዳዩን ለማጣራት የሚረዱ ተያያዥ ማስረጃዎችን አያይዞ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

9.2 ቦርዱ ሪፖርት ለቀረበበት ተጫራቾች ወይም አቅራቢ በቀረበበት ሪፖረት ላይ ያለውን ማስረጃ እና ማብራሪያ በ5 የስራ ቀናት ውስጥ ቢሮው እንዲያቀርብ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ይልካል፡፡

9.3 ቦርዱ ከሁለቱም ወገን የቀረበለትን መግለጫና ማስረጃዎች አጣርቶ ሪፖርቱ በቀረበበ 15 ሥራ ቀናት ውስጥ ውሳኔውን በጽሁፍ ለመ/ቤቱና ለተጫራቹ /ለአቅራቢው እንደ አስፈላጊነቱም ለሌሎች የሚመለከታቸው አካላት መላክ አለበት፡፡

9.4 ቦርዱ ለአቅራቢው የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ እንዲደርሰው ከማድረግ ጀምሮ ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ በመንግስት ግዥ እንዳይሳተፍ ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል፡፡